## መልዕክት ከአስተዳዳሪው፣

የኢቦላ ቫይረስ በሽታ (EVD)፣ የኢቦላ የደም መፍሰስ እና ትኩሳት (EHF)፣ ወይም ባጭሩ ኢቦላ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1976 ዓ.ም. በሰዎች ላይ የታየ፣ በሰዎች እና በእንስሶች ላይ በኢቦላ ቫይረስ የሚከሰት በሽታ ነው። የ2014 ዓ.ም. የኢቦላ ተላላፊ በሽታ በታሪክ ከፈተኛው ሲሆን፣ በምሥራቅ አፍሪካ ሶሥት አገሮችን በተለይ ሴራ ሊዮን፣ ጊኒ እና ላይቤሪያን በማጥቃት ላይ ያለ በሽታ ነው።

የዲሲ የጤና መምሪያ እና አጋሮቹ በኮሎምብያ ዲስትሪክት ሊከሰቱ በሚችሉ ሁኔታዎች ላይ መፍትሄ ለመስጠት ዝግጁነትን ለማረጋገጥ ጥንቃቄ እያደረጉ ነው። በከተማዋ ከሚገኙ የማህበረ ሰብ አጋሮች እንዲሁም ሆስፒታሎች፣ ክሊኒኮች፣ ላብራቶሪዎች እና ሌሎች የጤና እንክብካቤ ሰጭዎች ጋር ቅድመ ዝግጅት እያደረግን ነው። በተጨማሪም ከፌደራል እና ዓለም አቀፍ አጋሮቻችን፣ ሴንተር ፎር ዲዚዝ ኮንትሮል (CDC)፣ ዋይት ሀውስ፣ የጤና እና የሰብዓዊ አገልግሎቶች (HHS)፣ የሆስፒታል ማህበሮች፣ የዓለም የጤና ድርጅት (WHO)፣ የፓን አሜሪካን የጤና ድርጅት (PAHO)፣ የንግድ አጋሮችን ጨምሮ በሽታውን ለመቆጣጠር የተሻሉ አሠራሮችን በመካፈል የቅርብ ትብብር እያደረግን ነው።

**ስለ ኢቦላ በተሻለ መንገድ ለመረዳት መታወቅ ያለባቸው ቁልፍ ሁኔታዎች፣**

- **ኢቦላ በአሜሪካ በተፈጥሮ የሚከሰት በሽታ አይደለም**
- **በኮሎምብያ ዲስትሪክት የተከሰቱ የኢቦላ በሽታዎች የሉም**
- **ኢቦላን የመሳሰሉ የህዝብ የጤና ጉዳዮችን ለመቆጣጠር ዲስትሪክቱ ዝግጁ እና የተሟላ ነው**
- **ኢቦላ በዓየር የሚተላለፍ እና በጉንፋን ወይም በኢንፍሉዌንዛ የሚተላለፍ አይደለም**

ስለ ኢቦላ እንዲረዱ ትምህርታዊ እና ቴክኒካዊ መረጃዎችን እንሰጣለን። በተጨማሪም በጤና መምሪያ (DOH) ድህረ ገጽ የተሰጡ መረጃዎችን ለማጠናከር የአጋር ኤጅንሲዎች ድህረ ገጾች መገናኛዎችን እንሰጣለን። የኢንፍሉዌንዛ መርፌ እንድትወጉ እና እራስዎን በበለጠ ለመጠበቅ የመከላከያ ክትትልዎን በየጊዜው እንዲያደርጉ እንገፋፋለን።

የኮሎምብያ ዲስትሪክት ነዋሪዎችን እና በከተማችን የሚሠሩ እና የሚጫወቱትን ጤና እና ደህንነት ለመጠበቅ በቀደምትነት እንደምንሠራ እናረጋግጥልዎታለን።

ከመልካም ሰላምታ ጋር፣

ጆኤል ጋርሲያ፣ M.D., M.B.A
ዳይሬክተር እና ዋና የህክምና መኮንን